አንድም ፈቃዱ፡ ምሕረት፡ ይቅር፡ ባይ፡ ነውና፤

፲፱፤ ይትመየጠነ፡ ወይሣሃለነ፤

ከመዓት፡ ወደ፡ ምሕረት፡ ይመ ለስልናል፤ ይቅር፡ ይለናል፤

ወያሠጥሞን፡ ለኃጣውኢነ፡ ወይዌር ዖን፡ ውስተ፡ ቀላየ፡ ባሕር፡ ለአበሳነ፤

ትልቁን፡ ጥቃቅኑን፡ ኃጢአታ ችንን፡ በባሕር፡ ያሰጥመዋል፤ ከባሕር፡ የጣሉት፡ እንዳይታይ፡ አያስብብንም፡ ሲል ነው፤

፳፤ ወትሁቦ፡ ጽድቀ፡ ለያዕቆብ፡ ወሣህለ፡ ለአብርሃም፡ በከመ፡ መሐ ልከ፡ ለአበዊነ፡ በመዋዕለ፡ ትካት፤

ቀድሞ፡ ዘመን፡ ለአባቶቻችን፡ እንደማልህላቸው፤ ለአብርሃም፡ ይቅርታን፤ ለያዕቆብ፡ ቸርነት ህን፡ ትሰጣቸዋለህ፤ አንድም፡ ፈቃዱ፡ ምሕረት፡ ድኅነት፡ ዓለ ምን፡ የሚወድ፡ ነውና፡ ይትመ የጠነ፡ሰው፡ ሁኖ፤ ሥጋ፡ ለብሶ፡ ከመዓት፡ ወደምሕረት፡ ይመ ለስልናል፤ ወያሰጥሞን፡ በጥ ምቀት፤ በሥጋው፤ በደሙ፡ ኃጢአታችንን፡ ያስተሠርይል ናል፤ ወትሁቦ፤ ለያዕቆብ፡ ዘነ ፍስ፤ የምግባሩን፡ ዋጋ፡ ትሰ ጠዋለህ፤ በከመ፡ መሐልከ፡ በሐ ሙስ፡ ዕለት፡ ብለህ፡ እንደ ማልህ፡ እንደተናገርህ፤

ተፈጸመ፡ ዘሚክያስ፡ ነቢይ፤

ሚክያስ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ደረሰ፡ ተፈጸመ፤

በረከተ፡ አምላኩ፡ ትኩን፡ ምስሌነ፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፤

አነቃቅቶ፡ ላስጀመረን፡ አተጋ ግቶ፡ ለአስፈጸመን፡ ለእግዚአ ብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግ ባው፡ አሜን፡፡

የግል ቤተ መጻሕፍት

# ዘኢዩኤል ነቢይ፤

## መቅድም

ኢዩኤል፡ ማለት፡ ኄሩይ፡ እግ ዚአብሔር፤ አንድም፡ ኄሩየ፡ እግዚአብሔር፡ ማለት፡ ነው፤ ነገዱ፡ ከነገደ፡ ሮቤል፡ ነው፤ አባቱ፡ ባቱኤል፤ እናቱ፡ መር ሱላ፡ ትባላለች፤ መነሣቱ፡ በኢ ዮአታም፡ ዘመን፡ ነው፤ ይህ፡ አርእስት፡ ነው፤ ሠለስቱ፡ ምዕት፡ ለመጻሕፍት፡ አርእ ስት፡ ሲሰጡ፡ አርእስት፡ ሰጥ ተውታል፤ እርሱ፡ ግን፡ ነገ ሩን፡ ቃለ፡ እግዘአብሔር፡ ዘኮነ፡ ኀበ፡ ኢዩኤል፡ ወልደ፡ ባቱ ኤል፡ ብሎ፡ ያመጣዋል፤

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኮነ፡ ኀበ፡ ኢዩኤል፡ ወልደ፡ ባቱኤል፤

ዘመጽአ፡ ዘተነግረ፡ ሲል፡ ነው፤ ከባቱኤል፡ ልጅ፡ ከኢዩኤል፡ ዘንድ፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግ ዚአብሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤

፪፤ ስምዑ፡ ዘንተ፡ ሊቃውንተ፡ ቤተ፡ እስራኤል፤

የእስራኤል፡ ወገኖች፡ አለቆች፡ ይኸን፡ ነገር፡ ስሙ፤

ወአፅምዑ፡ ኵልክሙ፡ እለ፡ ትነብሩ፡ ውስተ፡ ምድር፤

በዚህ፡ ዓለም፡ የምትኖሩ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ስሙ፤

ለእመ፡ ከዊነ፡ ኮነ፡ ከመዝ፡ በመ ዋዕሊክሙ፤

በዘመናችሁ፡ እንዲህ፡ ያለ፡ ነገር፡ ተደርጎ፡ እንደሆነ፤

ወበመዋዕለ፡ አበዊክሙ፤

በአባቶቻችሁም፡ ዘመን፡ እን ዲህ፡ ያለ፡ ነገር፡ ተደርጎ፡ እንደሆን፤

፫፤ ከመ፡ ትንግሩ፡ ለደቂቅክሙ፤

እናንተ፡ ለልጆቻችሁ፡ ትነግሩ፡ ዘንድ፤

ወደቂቅክሙኒ፡ ለደቂቆሙኒ፤

ልጆቻችሁም፡ ለልጆቻቸው፡ ይነግሩ፡ ዘንድ፤

ወደቂቆሙ፡ ለካልዕ፡ ትውልድ፤

ልጆቻቸው፡ ለሌላ፡ ትውልድ ይነግሩ፡ ዘንድ፡ አራተኛ፡ ትው ልድ፡ ይሆናል፤

፬፤ ዘአትረፈ፡ ዕፄ፡ በልዓ፡ አንበጣ፤

ለእመ፡ ከዊነ፡ ኮነ፡ ያለውን፡ አመጣ፤ ከትል፡ የቀረውን፡ አን በጣ፡ በላው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወዘአትረፈ፡ አንበጣ፡ በልዖ፡ ደጎብያ፤

ከአንበጣ፡ የቀረውን፡ ኩብኩባ፡ በላው፤ እራሪው፡ የቀረውን፡ ማለት፡ አይደለም፤ በልቶለት፡ የቀረውን፡ ማለት፡ ነው፤

ወዘአትረፈ፡ ደጎብያ፡ በልዓ፡ አናኵዕ፤

ከኩብኩባ፡ የቀረውን፡ ችግኝ፡ (ተምች)፡ በላው፤ አንድም፡ ከፉሃ፡ የቀረውን፡ ቴልጌል፤ ከቴልጌል፡ የቀረውን፡ ስልምናሶር፤ ከስልምና ሶር፡ የቀረውን፡ ናቡከደነፆር፡ ያጠፋዋል፤

፭፤ ነስሑ፡ እንከ፡ እለ፡ ትሰትዩ፡ ወይነ፤

ወይን፡ የምትጠጡ፡ ሰዎች፡ እዘኑ፤

ብክዩ፡ ወላህዉ፡ ኵልክሙ፡ እለ፡ ትሰትይዎ፡ ለወይን፡ ለሰኪር፤

ለመስከር፡ ወይንን፡ የምትጠጡ፡ ሰዎች፡ እዘኑ፤ አልቅሱ፤ ለቁመተ፡ ሥጋ ያህል፡ ቢጠጡ፡ እዳ፡ አይሆንምና፤ ለሰኪር፡ አለ፤

እስመ፡ ተሠዕረ፡ ፍሥሓ፡ ወሐሤት፡ እምአፉክሙ፤

በግብሩ፡ ወይንን፡ ሐሤት፡ ብሎታል፤ አንድም፡ የአፍ፡ ተድላ፡ ደስታው፡ መብል፡ መጠጥ፡ ነው፤ መብል፡ መጠጥ፡ ካፉቸው፡ ጠፍቷልና፤

፮፤ እስመ፡ ዓርገ፡ ሕዝብ፡ ጽኑዓን፡ ውስተ፡ ምድርክሙ፡ ዘአልቦሙ፡ ኍልቍ፤

ቍጥር፡ ስፍር፡ የሌላቸው፡ ጽኑዓን፡ አሕዛብ፡ ወደሀገራችሁ፡ ስለመጡ፤

ስነኒሆሙ፡ ስነ፡ አናብስት፤

ጥርሳቸው፡ እንደ አንበሳ፡ ጥርስ፡ ነው፡ ማለት፡ ሥልጣናቸው፡ ጽኑ፡ ነው፤

ወኵርናአቲሆሙ፡ ዘዕጓለ፡ አናብስት፤

ክንዳቸው፡ እንደ፡ አንበሳ፡ ወይፈን፡ ነው፡ ማለት፡ ሥልጣናቸው፡ ጽኑ፡ ነው፤

፯፤ ረሰይዎ፡ ምድረ፡ ለወይንየ፤

ወይኔን፡ እንደ፡ ምድር፡ ረገጡት፤ ባለቤት፡ የሆነ፡ እንደ ሆነ፡ ሐረጉ፡ እንዳይቈረጥ፡ ቅጠሉ፡ እንዳይበጠስ፡ አድርጎ፡ ተጠንቅቆ፡ ይለቅመዋል፤ እሊህ፡ ግን፡ ሐረጉን፡ ቆርጠው፡ ቅጠሉን፡ በጥሰው፡ ፍሬውን፡ ለቅመው፡ ሔደዋልና፤ አንድም፡ ወገኖቼ፡ እስራኤልን፡ አዋረዱ፤

ወሠበሩ፡ በለስየ፤

በለሴን፡ ሰበሩ፤ አንድም፡ ቤተ፡ እስራኤልን፡ አጠፉ፤ በለስ፡ ዘይቤ፡ ቤተ፡ እስራኤል፡ እሙንቱ፡ እንዲል፤



ወኃሠሠ፡ ወፈተነ፡ ወገደፉ፤

እየመረመሩ፡ አጠፏት፤

በዘአፃዕደወት፡ ምድር፡ አዕፁቂሃ፤

ኢየሩሳሌም፡ መከሯን፡ በአደረሰች፡ ጊዜ፤ አንድም፡ ቤተ፡ እስራኤል፡ ተድላ፡ ደስታዋን፡ ባደረገች፡ ጊዜ፡ እየመረመሩ፡ አጠፏት፤

፰፤ ትብኪ፡ መርዓት፤

ሙሽራዪቱ፡ ታልቅስ፤

ወትቅንት፡ ሠቀ፡ በእንተ፡ ምታ፡ ዘድንግልናሃ፤

በድንግልናዋ፡ ስለአገባችው፡ ባሏ፡ ሞት፡ ምንጣፍ፡ ትታጠቅ፤

፱፤ ተሠዕረ፡ መሥዋዕት፡ ወሞጻሕት፡ እምቤተ፡ እግዚአብሔር፤

ከቤተ፡ እግዚአብሔር፡ ወይኑ፡ መሥዋዕቱ፡ ጠፋ፤

ላህዉ፡ ወቅንቱ፡ ሠቀ፡ ካህናት፡ እለ፡ ትሠውዑ፡ መሥዋዕተ፡ ውስተ፡ አቅርንተ፡ ምሥዋዕ፤

በአቅርንተ፡ ምሥዋዕ፡ ያላችሁ፤ አንድም፡ በአቅርንተ፡ ምሥዋዕ፡ ስቡን፡ የምትመሉ፡ ካህናት፡ ማቅ፡ ታጠቁ፤ እዘኑ፤

፲፤ እስመ፡ ኃሠረ፡ ገራውህ፤

እርሻው፡ ጠፍቷልና፤

ወትላሁ፡ ምድር፤

ትሑታኑ፡ ይዘኑ፤

እስመ፡ ኃሠረ፡ ዕክል፡ ወየብሰ፡ ወይን፤

እህሉም፡ ወይኑም፡ ደርቋልና፤

ወጠፍዓ፡ ዘይት፤

ዘይቱም፡ ጠፍቷልና፤

፲፩፤ ወተሐፍሩ፡ ሐረስት፤

አራሾች፡ አፈሩ፤

ወበከዩ፡ ዓቀብተ፡ ወይን፡ በእንተ፡ ሥርናይ፡ ወሰገም፤

ገብሱ፤ ስንዴው፡ ስለጠፋ፡ ወይን፡ ጠባቆች፡ አለቀሱ፤

እስመ፡ ጠፍዓ፡ ማዕረር፡ እምገራውህ፤

አዝመራው፡ ከእርሻ፡ ጠፍቷልና፤

፲፪፤ ወየብሰ፡ ወይን፤

ወይኑም፡ ደርቋልና፤

ወሐልቀ፡ በለስ፡ ወሮማን፡ ወተምር፡ ወኮል፡ ወኵሉ፡ አቅማሐ፡ ገዳም፤

በለስ፡ ሮማን፡ ተምር፡ እንኮይ፡ በምድረ፡ በዳ፡ ያለው፡ ተክል፡ ሁሉ፡ ጠፍቷልና፡ እዘኑ፤

ወተኃፍረ፡ ፍሥሐሆሙ፡ ለደቂቀ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፤

የሰዎች፡ ሁሉ፡ ተድላ፡ ደስታቸው፡ ጠፋ፤

፲፫፤ ላህዉ፡ ወቅንቱ፡ ሠቀ፡ ካህናት፤

ካህናቱም፡ ማቅ፡ ታጥቃችሁ፡ እዘኑ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወብክዩ፡ እለ፡ ትትለአኩ፡ መሥዋዕተ፡ ለእግዚአብሔር፤

ለእግዚአብሔር፡ መሥዋዕቱን፡ የምትሠዉ፡ ካህናት፡ አልቅሱ፤

እስመ፡ ሐልቀ፡ መሥዋዕት፡ ወሞጻሕት፡ እምቤተ፡ እግዚአብሔር፤

መሥዋዕቱም፡ ወይኑም፡ ከቤተ፡ እግዚአብሔር፡ ጠፍቷልና፤

፲፬፤ ቀድሱ፡ ጾመ፤

ጾም፡ እንጹም፡ ብላችሁ፡ ለዩ፤

ወስብኩ፡ ምሕላ፤

ምሕላ፡ እንያዝ፡ ብላችሁ፡ አዋጅ፡ ንገሩ፤

አስተጋብዑ፡ ሊቃውንተ፤

ሊቃውንቱን፡ ሰብስቡ፡ ሕፃናቱም፡ ይላል፤

ወኵሎ፡ ዘይነብር፡ ውስተ፡ ምድር፡ ውስተ፡ ቤተ፡ አምላክነ፤

በኢየሩሳሌም፡ የሚኖረውን፡ ሰው፡ ሁሉ፡ በፈጣሪያችን፡ ማደሪያ፡ በቤተ መቅደስ፡ ሰብስቡ፤

ወጽርሑ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ ኅቡረ፤

አንድ፡ ሁናችሁ፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ለምኑ፤

፲፭፤ አሌ፡ ለክሙ፡ ይእቲ፡ አሚረ፤

ያን፡ ጊዜ፡ ወዮላችሁ፤

እስመ፡ አልጸቀት፡ ዕለተ፡ እግዚአብሔር፤

እስራኤል፡ የሚማረክባት፡ ቀን፡ ደርሳለችና፤

ወከመ፡ እምነ፡ መቅሠፍት፡ ውስተ፡ መቅሠፍት፡ ይመጽእ፡ በቅድመ፡ አዕይንቲክሙ፤

እንዱን፡ መቅሠፍት፡ ከማየም ጣት፤ እንዱን፡ መቅሠፍት፡ ወደ ማምጣት ይመጣል፤

፲፮፤ ወይጠፍዕ፡ እምቤተ፡ አምላክነ፡ ፍሥሓ፡ ወሐሤት፤

ከፈጣሪያችን፡ ማደሪያ፡ ከቤተ፡ መቅደስ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ይጠፋል፤

፲፯፤ ዕጐልት፡ በውስተ፡ ሕዝአቆን፡ ጠፍዓ፤

ላሞች፡ ከበረታቸው፡ ጠፉ፤ አንድም፡ መምህራን፡ ከጉባዔ፡ ታጡ፤

ወሐልቁ፡ መዛግብት፡ ወተነሥቱ፡ ምክያዳት፤

ጐታው፤ ጐተራው፡ ጠፋ፤ ፈረሰ፤

እስመ፡ የብሰ፡ ዕክል፤

እህሉ፡ ደርቋልና፤ አንድም፡ ዘአትረፈ፡ ዕፄ፡ በልዓ፤ አንበጣ፡ ብዬ፡ እንደተናገርሁ፤

፲፰፤ ምንተ፡ ይሬሲ፡ ለነ፤

ምን፡ ያደርግልናል፤

በከዩ፡ አቃብያነ፡ ላህም፡ እስመ፡ ሐልቀ፡ መርዔቶሙ፤

ላም፡ የሚጠብቁ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ አለቀሱ፤ ብዙ፡ ከብታቸው፡ ጠፍቷልና፤



ወጠፍዓ፡ መራዕየ፡ አባግዕ፤

የበጉ፡ መንጋ፡ ጠፍቷልና፤

፲፱፤ ኀቤከ፡ እጸርሕ፡ እግዚኦ፤

አቤቱ፡ ካንተ፡ ዘንድ፡ እለምናለሁ፤

እስመ፡ እሳት፡ አኅለቀት፡ ስነ፡ ገዳም፤

ድርቅ፡ በምድረ፡ በዳ፡ ያለውን፡ አበባ፡ አጥፍቷልና፤

ወነበልባል፡ አውዓየ፡ ዕፀ፡ ወያመ፤

ድርቅ፡ ታላላቁን፡ ጥቃቅኑን፡ ዛፍ፡ አጥፍቷልና፤

፳፤ ወአንቃዕደዉ፡ ኀቤከ፡ እንስሳ፡ ሐቅል፤

በምድረበዳ፡ ያሉ፡ እንስሳት፡ ወደ፡ አንተ፡ ይለምናሉ፤ እሱ፡ ባወቀ፡ ይለምኑታልና፤

ወሐልቁ፡ ወየብሱ፡ አንቅዕተ፡ ማያት፤

የውሆች፡ ምንጮች፡ ፈጽመው፡ ደረቁ፤

ወበልዓት፡ እሳት፡ ስነ፡ ገዳም፤

ድርቅ፡ በምድረበዳ፡ ያለውን፡ ሁሉ፡ አጠፋች፤ አንድም፡ እስመ እሳት፡ አሕለቀት፡ ስነ፡ ገዳም፤ ጦር፡ ቸነፈር፡ ሰውን፡ ሁሉ፡ አጥፍታለችና፡ ወደ፡ አንተ፡ እጮሃለሁ፤ እንስሳ፡ ሐቅል፡ እስራኤል፡ ወደ፡ አንተ፡ ይለምናሉ፤ እስመ፡ የብሱ፡ የት [illegible] ነብ ያት፡ ካህናት፡ ጠፍተዋል፡ ሙተዋልና፡ ወበልአት፤ የኢየሩሳሌም፡ ጌጥ፡ ሽልማት፡ የሆኑ፡ እስራኤልን፡ ጦር፡ ቸነፈር፡ አጥፍታለችና።

## ምዕራፍ ፪

፩፤ ንፍሑ፡ ቀርነ፡ በጽዮን፤

በጽዮን፡ ነጋሪቱን፡ ምቱ፡ ጦር፡ ለመሰብሰብ፡ አንበጣ፡ ለመከልከል፤

ወስብኩ፡ በደብረ፡ መቅደስየ፤

በቤተ፡ መቅደስ፡ ምህላ፡ ለመያዝ፡ አዋጅ፡ ንገሩ፤

ወይደንግፁ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ውስተ ዓለም፤

በዚህ፡ ዓለም፡ ያሉ፡ ሁሉ፡ ይደንግጡ፤

እስመ፡ አልጸቀት፡ ዕለተ፡ እግዚአብሔር፡ ወበጽሐት፤

እስራኤል፡ የሚማረክባት፡ ቀን፡ ደርሳለችና፤

፪፤ ዕለተ፡ ጽልመት፡ ወዓውሎ፤

ጨለማ፡ ጥቅል፡ ነፋስ፡ የሚመጣባት፡ ቀን፡ ናትና፤

ዕለተ፡ ደመና፡ ወጊሜ፤

ደመና፡ የተረገረገባት፤ ጉም፡ የሚሳብባት፡ ቀን፡ ናትና፤ አንድም፡ የመከራ፡ ቀን፡ ናትና፤

www.ethiopianorthodox.org

ከመ፡ ጎህ፡ ይዘረዉ፡ ሕዝብየ፡ ብዙ
ኃን፡ ውስተ፡ አድባር፡ በመዓት፡ ዕኑዕ፡
ዘኢኮነ፡ ከማሁ፡ እምፍጥረተ፡ ዓለም፤

ዓለም፡ ከተፈጠረ፡ ጀምሮ፡ ተደ
ርጎ፡ በማያውቅ፡ በጽኑ፡ መከራ፡
ተይዘው፡ ወገኖቼ፡ እንደ፡ ጎህ፡
(እንደ ንጋት) በተራራው፡
ይበተናሉ፤

ወኢይደግም፡ እንከ፡ እምድኅሬሁ፡
እስከ፡ አመ፡ ትውልደ፡ ትውልድ፤

ከዚህም፡ በኋላ፡ እንግዲህ፡ ወዲ
ህም፡ እስከ፡ ልጅ፡ ልጅ፡ ዘመን፡
በማይደረግ፡ በጽኑ፡ መከራ፡
ተይዘው፡ ይበተናሉ፤

፫፤ በፍጽምሂ፡ እሳት፡ ይበልዕ፡
ወበከዋላሂ፡ ያውዒ፡ ነበልባል፤

ድርቅ፡ ከፊት፡ በር፡ እስከ፡ ኋላ፡
ዳረገንድ፡ ድረስ፡ ያጠፋል፤ አን
ድም፡ በፊት፡ የደረሰውን፡
በፊት፤ በኋላ፡ የደረሰውን፡
በኋላ፡ ያጠፋል፤ አንድም፡
በስልምናሶር፡ በናቡከደነፆር፡
ያጠፋል፤ አብነት፡ በድልቅልቅ፡
ወበዓውሎ፡ ፍኖቱ፡ ይላል፤

ከመ፡ ገነተ፡ ኤዶም፡ ምድር፡ ቀዳሚሃ፤

ጥንቱን፡ ኢየሩሳሌም፡ እንደ፡
ገነት፡ ነበረች፤

ወትገብዕ፡ ድኅሬሃ፡ ከመ፡ በድወ፡
ሐሩር፤

ኋላ፡ ምድረ፡ በዳ፡ ወደመሆን፡
ትመለሳለች፤

ወአልቦ፡ ዘየመሥጥ፡ እምእዴሆሙ፤

ከነዚያ፡ የሚያመልጥ፡ የለም፤

፬፤ ከመ፡ ገጸ፡ ፈረስ፡ ገጸሙ፤

አሕዛብ፡ እንደፈረስ፡ ፊታቸው፡
የተነፋፋ፡ ነው፤

ወረዋጽያን፡ ከመ፡ አፍራስ፤

እንደፈረስ፡ ፈጣኖች ናቸው፤

፭፤ ወድምፆሙ፡ ከመ፡ ድምፀ፡
ሠረገላ፡ ዘይሜርድ፡ ውስተ፡ አድባር፤

ድምፃቸውም፡ በተራራ፡ እንደ
ሚሄድ፡ ሠረገላ፡ ድምፅ፡ ነው፤

ያ፡ እንዲአስፈራ፡ ያስፈራል፤

ወከመ፡ ድምፀ፡ ነበልባለ፡ እሳት፡ እንተ፡
ትበልዕ፡ ብርዓ፤

ገለባውን፡ እንደምታቃጥል፡ እን
ደቋያ፡ እሳት፡ ድምፅ ነው፤

ወከመ፡ ሠራዊት፡ ብዙኃን፡ ወጽኑዓን፡
እለ፡ ይትቃተሉ፡ ውስተ፡ ሙራድ፤

ሊወጉ፡ በሄዱበት፡ ጸንተው፡
እንደሚዋጉ፡ እንደ፡ ብዙ፡ ሠራ
ዊት፡ ድምፅ፡ ነው፤ ያ፡ እንደ
ሚያስፈራ፡ ያስፈራል፤



፮፤ ወይትቀጠቀጡ፡ አሕዛብ፡ እም
ቅድመ፡ ገጹ፤

ከገጹ፡ መዓቱ፡ የተነሣ፡ አሕ
ዛብ፡ ይጠፋሉ፤

ወይከውን፡ ገጸ፡ ኵሎሙ፡ ከመ፡ ጸለሎ፡
መቅፁት፤

የሰው፡ ሁሉ፡ ፊት፡ እንደ፡ ድስት፡
ጥላት፡ ይሆናል፤

፯፤ ወይረውጹ፡ ከመ፡ መስተቃት
ላን፡ ወከመ፡ ዕደው፡ ተባዕያን፡ የዓ
ርጉ፡ ዓረፍተ፤

አርበኞች፡ እንደመሆናቸው፡
ጸንተው፡ እንደሚዋጉ፡ ሰዎች፡
ይገሰግሣሉ፤ ቅጽሩን፡ እየዘለሉ፡
ይገባሉ፤

ወኵሎሙ፡ እንከ፡ የሐውሩ፡
በፍኖቶሙ፤

ሁሉም፡ በየጐዳናቸው፡ ይሄዳሉ፤

ወኢይትገሐሡ፡ እምፍኖቶሙ፤

ከጐዳናቸው፡ ጥቂት፡ ፈቅ፡
አይሉም፤

፰፤ ወኢይትረኃቁ፡ አሐዱ፡
እምካልዑ፤

አንዱ፡ ካንዱ፡ አይራራቁም፤
እጅ፡ለእጅ፡ተያይዘው፡ ይሄዳሉ፤

ጽውራኒሆሙ፡ ንዋየ፡ ሐቅሎሙ፡
ይረውፁ፤

ጋሻ፡ ጦራቸውን፡ ይዘው፡
ይሄዳሉ፤

ወያኃልቁ፡ በሐያሙ፤

በፍላፃቸው፡ ሰውን፡ ያጠፋሉ፤

፱፤ ወያስተጋብዑ፡ አህጉረ፤

አገሩን፡ ሁሉ፡ እጅ፡ ያደርጋሉ፤

ወይረውፁ፡ ዲበ፡ ዓረፍት፡ ወይበውዑ፡
እንተ፡ መሳክው፡ ከመ፡ ሰረቅት፤

እንደሌቦች፡ ቅጽሩን፡ እየዘለሉ፡
በመስኮት፡ ይገባሉ፤

፲፤ ወትደነግፅ፡ ምድር፡ እም
ቅድመ፡ ገጸሙ፤

ከፊታቸው፡ የተነሣ፡ ትሑታኑ፡
ይደነግጣሉ፤

ወያድለቀልቅ፡ ሰማይ፤

ሰማይም፡ ይነዋወጣል፡ ማለት፡
ልዑላኑ፡ ይነዋወጣሉ፤

ወይጸልም፡ ፀሐይ፡ ወወርህ፤

ንጉሡ፤ ቢትወደዱ፡ በመከራ፡
ይጠቁራሉ፤

ወይጠፍዕ፡ ብርሃኖሙ፡ ለከዋክብት፤

የሠራዊቱ፡ ተድላ፡ ደስታ፡
ይጠፋል፤

፲፩፤ ወይሁብ፡ እግዚአብሔር፡ ቃሎ፡
እምቅድመ፡ ገጸ፡ ኃይሉ፤

እግዚአብሔርም፡ ከኃይሉ፡ መገ
ለጥ፡ የተነሣ፡ እነሰናክሬም፡
ይጥፉ፤ እስራኤል፡ ይዳኑ፡
የሚል፡ ትእዛዙን፡ ይሰጣል፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፯። ወይብክዩ፡ ካህናት፡ እለ፡ ይሠውዑ፡ ለእግዚአብሔር፡ በማዕከለ፡ አቅርንተ፡ ምሥዋዕ።

በአቅርንተ፡ ምሥዋዕ፡ መካከል፡ ለእግዚአብሔር፡ መሥዋዕት፡ የሚያቀርቡ፡ ካህናትም ያልቅሱ። አንድም፡ የሚሠዉ፡ ካህናት፡ አቅርንተ፡ ምሥዋዑን ይዘው ያልቅሱ።

ወይበሉ፡ መሐክ፡ እግዚኦ፡ ሕዝበከ።

አቤቱ፡ ወገኖችህን፡ ይቅር፡ በላቸው፡ ይበሉ።

ወኢታኅሥር፡ ርስተከ።

ማደሪያዎችህ፡ እስራኤልን፡ አታዋርዳቸው፡ አታጕሳቁላቸው።

ከመ፡ ኢይንጽሕዎሙ፡ አሕዛብ።

አሕዛብ፡ በመከራ፡ እንዳይጥሏቸው።

ወኢይበሉ፡ አይቴ፡ ውእቱ፡ አምላኮሙ።

ፈጣሪያቸው፡ አያድናቸው፡ አይረዳቸው፡ወዴት፡አለ፡እንዳይሉ።

፲፰። ወቀንአ፡ እግዚአብሔር፡ ለምድሩ፡ ወመሐኮሙ፡ ለሕዝቡ።

እግዚአብሔር፡ ለሀገሩ፡ ለኢየሩሳሌም፡ ቀንቶ፡ ለወገኖቹ፡ ራሩላቸው።

፲፱። ወተሰጥዎሙ፡ እግዚአብሔር፡ ወይቤሎሙ፡ ለሕዝቡ፡ ናሁ፡ አነ፡ እፌኑ፡ ለክሙ፡ እክለ፡ ወወይነ፡ ወዘይተ፡ ወትፀግቡ።

እግዚአብሔር፡ ወገኖቹን፡ በረድኤት፡ ተቀበላቸው። እነሆ፡ ወይኑን። እህሉን። ዘይቱን፡ እሰጣችኋለሁ፡ ትጠግባላችሁ፡ አለ።

ወኢይሬስየክሙ፡ ዕዕለተ፡ ለአሕዛብ።

ለአሕዛብ፡ ስድብ፡ አላደርጋችሁም።

፳። ወእሰድዶሙ፡ እምኔክሙ፡ ለእለ፡ መንገለ፡ ሰሜን።

የባቢሎንን፡ ሰዎች፡ ከናንተ፡ ለይቼ፡ አስማርኬ፡ እሰድዳቸዋለሁ። ምነው፡ ኢየሩሳሌም፡ ምሥራቅ፡ አይደለችም? ቢሉ፡ አራት፡ መዓዝን፡ የሌለውን፡ አለ? ለአንዱ፡ ምሥራቅ፡ ብትሆን፡ ላንዱ፡ ሰሜን፡ ትሆናለች። አንድም፡ እመንገለ፡ ሰሜን፡ እንደማለት፡ ከፋርስ፡ ከባቢሎን፡ አጠፋችኋለሁ።

ወእወስዶሙ፡ ውስተ፡ ምድረ፡ በድው።

በፋርስ፡ አውራጃ፡ ወዳለው፡ ምድረ፡ በዳ፡ አጠፋቸዋለሁ።



ወእሠጥሞሙ፡ ውስተ፡ ቀዳሚት፡ ባሕር፡ ወውስተ፡ ደኃሪት፡ ባሕር።

ከፊት፡ በር፡ እስከ፡ ኋላ፡ ዳረገንድ፡ የሰፈሩትን፡ አጠፋቸዋለሁ። አንድም፡ ታላቁንም፡ ታናሹንም፡ አጠፋዋለሁ። አንድም፡ በስልምናሶር፡ በናቡከደነፆር፡ አጠፋቸዋለሁ።

ወየዓርግ፡ ፂዓቱ።

ሽታው።

ወንስንቱ።

ክርፋቱ። ግማቱ። ከሩቅ፡ ይሸታል። ማለት፡ የሰናክሬም፡ ዜና፡ ጥፋቱ፡ ከሩቅ፡ ይሰማል።

እስመ፡ አዕበየ፡ ምግባሮ።

ሰናክሬም፡ ብልጣሶር፡ ራሱን፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አድርጓልና። አንድም፡ ኃጢአቱን፡ አብዝቷልና።

፳፩። ተአመኒ፡ ምድር።

ምድር፡ እመኚ።

ወተፈሥሒ፡ ወተሐሠዪ፡ እስመ፡ አዕበየ፡ እግዚአብሔር፡ ግብሮ፡ ከመ፡ ይግበር፡ ላዕሌኪ።

እግዚአብሔር፡ ይቅርታውን፡ ባንቺ፡ ላይ፡ ያደርግ፡ ዘንድ፡ አብዝቷልና። በውስጥ፡ በአፍአ፡ ደስ፡ ይበልሽ።

፳፪። ተአመኑ፡ እንስሳ፡ ገዳም።

በቁሙ፡ እንስሳት፡ ደስ፡ ይበላችሁ፡ እመኑ።

እስመ፡ ብዕለ፡ አሕቃላተ፡ በድው።

የምድረበዳ፡ አውራጃ፡ ሁሉ፡ በአዝርእት። በአትክልት። በልምላሜ፡ ከብረዋልና። አንድም፡ በምድረ፡ በዳ፡ የምትኖሩ፡ እስራኤል፡ እመኑ፡ ደስ፡ ይበላችሁ። ምድረበዳ፡ የነበሩ፡ የኢየሩሳሌም፡ አውራጃዎች፡ በብዕለ፡ አሕዛብ፡ ከብረዋልና።

ወፈረየ፡ ዕፅ።

ዛፉ፡ አፍርቷልና።

ወይን፡ ወበለስ፡ ወሀቡ፡ ኃይሎሙ።

ወይኑም፡ በለሱም፡ ፍሬያቸውን ሰጡ።

፳፫። ተፈሥሑ፡ ወተሐሠዩ፡ በእግዚአብሔር፡ አምላክክሙ፡ ደቂቀ፡ ጽዮን።

የጽዮን፡ ልጆች፡ በፈጣሪያችሁ፡ በእግዚአብሔር፡ አምናችሁ፡ በውስጥ፡ በአፍአ፡ ደስ፡ ይበላችሁ።

እስመ፡ ወሀበክሙ፡ ሲሳየ፡ ጽድቅ።

እውነተኛውን፡ ምግብ፡ ሰጥቷችኋልና።

www.ethiopianorthodox.org

ወያዘንም፡ ለክሙ፡ ፀደየ፡ ወመፀወ፤

የለቀውን፡ ዝናም፤ የመስከረሙን፤ የጥቅምቱን፡ ዝናም፡ ያዘንምላችኋል፤

፳፬፤ ከመ፡ ትካት፡ ይመልዕ፡ ዓውደ፡ እክል፤

የእህሉ፡ አውድማ፡ እንደ፡ ቀደመው፡ ይመላል፤

ወይትከዓው፡ ምክያዳተ፡ ወይን፡ ወዘይት፤

የወይኑ፡ የዘይቱ፡ አውድማ፡ መልቶ፡ ትርፍርፍ፡ ይላል፤

፳፭፤ ወእፈድየክሙ፡ ህየንተ፡ ዓመት፡ ዘበልዖ፡ አንበጣ፤

አንበጣ፡ ስለበላው፡ ዘመን፡ ፈንታ፡ እከፍላችኋለሁ፤

ወደጎብያ፤

ኩብኩባ፡ ስለበላው፡ ፈንታ፡ እከፍላችኋለሁ፤

ወዐዌ፤

ትል፡ ስለበላው፡ ፈንታ፤

ወአናኵዕ፤

ተምች፡ (ችግኝ)፡ ስለበላው፡ ፈንታ፤

ኃይልየ፡ ዘፈነውኩ፡ ላዕሌክሙ፤

በናንተ፡ ያመጣኋቸው፡ ሠራዊቶቼ፡ እነዚህ፡ ስለበሉት፡ ፈንታ፡ እከፍላችኋለሁ፤ አንድም፡ ቴልጌል፤ ስልምናሶር፤ ፉሃ፤ ናቡከደነፆር፡ ስለበሉት፡ ፈንታ፡ እከፍላችኋለሁ፡ ከሃሊነቴን፡ ታውቁ፡ ዘንድ፤

፳፮፤ ተሴሰዩ፡ ወብልዑ፡ ወዕግቡ፤

በልታችሁ፡ ጥገቡ፡ ዕኑ፤

ወሰብሑ፡ ለእግዚአብሔር፡ አምላክነ፤

ለፈጣሪያችን፡ ለእግዚአብሔር፡ ምስጋና፡ አቅርቡ፤

እስመ፡ ገብረ፡ ለክሙ፡ መንክረ፤

ለናንተ፡ ድንቅ፡ ሥራ፡ ሠርቶላችኋልና፤

ወኢይትሐፈሩ፡ እንከ፡ ሕዝብየ፡ ለዓለም፤

እንግዲህ፡ ወዲህ፡ ወገኖቼ መከራ፡ መጥቶባቸው፡ ለዘለዓለሙ፡ አያፍሩም፤

፳፯፤ ወተአምሩ፡ እንከ፡ ከመ፡ ሀሎኩ፡ አነ፡ ማዕከለ፡ እስራኤል፤

እኔ፡ በናንተ፡ መካከል፡ በረድኤት፡ እንዳለሁ፡ እወቁ፤

ወአነ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክክሙ፤

ፈጣሪያችሁ፡ እኔ፡ እንደሆንኩ፡ እወቁ፤

ወአልቦ፡ ባዕድ፡ አምላክ፡ ዘእንበሌየ፤

ከኔ፡ በቀር፡ ሌላ፡ ፈጣሪ፡ እንደሌለ፡ ታውቃላችሁ፤



ወኢይትሐፈሩ፡ እንከ፡ ኵሉ፡ ሕዝብየ፡ ለዓለም፤

ወገኖቼ፡ ሁሉ፡ መከራ፡ መጥቶባቸው፡ ለዘለዓለሙ፡ አያፍሩም፤

## ጉባዔ

፳፰፤ ወእምድኅረ፡ ዝንቱ፡ እክዑ፡ እምነ፡ መንፈስየ፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ ዘሥጋ፤

ከሰባ፡ ዘመን፡ በኋላ፡ ረድኤቴን፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ በሥጋዊ፡ በደማዊ፡ ሁሉ፡ አሣድራለሁ፤

ወይትኔበዩ፡ ደቂቅክሙ፡ ወአዋልዲክሙ፤

ወንዶች፡ ልጆቻችሁ፡ ሴቶች፡ ልጆቻችሁ፡ ትንቢት፡ ይናገራሉ፤

ወሊቃውንቲክሙ፡ ሕልመ፡ የሐልሙ፤

እነዳንኤል፡ እነዕዝራ፡ ሕልም፡ ያያሉ፤

ወወራዙቲክሙ፡ ራእየ፡ ይሬእዩ፤

እነሕዝቅኤል፡ እነኢሳይያስ፡ ራእይ፡ ያያሉ፤

፳፱፤ ወላዕለ፡ አግብርትየ፡ ወአዕማትየ፡ ይእተ፡ አሚረ፡ እክዑ፡ እምነ፡ መንፈስየ፤

በወንዶች፡ ባሮቼ፤ በሴቶች፡ ባሮቼ፡ ላይ፡ ረድኤቴን፡ አሳድራለሁ፤ አንድም፡ ወእምድኅረ፡ ዝንቱ፡ እክዑ፡ እምነ፡ መንፈስየ፡ ብለህ፡ መልስ፤ አምስትሺህ፡ ካምስት፡ መቶ፡ ዘመን፡ በኋላ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ በፍጥረቱ፡ ሁሉ፡ አሳድራለሁ፤ እንዲህ፡ ስላለ፡ ግን፡ በሁሉ፡ የሚያድር፡ ሆኖ፡ አይደለም፤ ወዝንቱ፡ ንባብ፡ ኢይበጽሕ፡ ላዕለ፡ ኵሎሙ፡ ለባስያነ፡ ሥጋ፡ እንዲል፤ ወንዶች፡ ልጆቻችሁ፡ እነአጋቦስ፡ ትንቢት፡ ይናገራሉ፤

ወነሥአ፡ ቅናቶ፡ ለጳውሎስ፡ ወተአሥረ፡ እደዊሁ፡ ወእገሪሁ፡ ወይቤ ለበዓለዝ፡ ቅናት፡ የአሥርዎ፡ አይሁድ፡ በኢየሩሳሌም፡ ብሎ እንደ፡ ተናገረ፤ ሴቶች፡ ልጆቻችሁ፡ ትንቢት፡ ይናገራሉ፤ አዋልደ፡ ፊልጶስ፡ አርባዕ፡ የሚላቸው፤ እነጴጥሮስ፡ በናኅሰ፡ ኢዮጴ፡ ቋሚ፡ ሕልም፡ ያያሉ፤ እነዮሐንስ፡ በደሴተ፡ ፍጥሞ፡ ራእይ፡ ያያሉ፤ በአርድዕት፡ ላይ፡ በቅዱሳት፡ አንስት፡ ላይ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ አሣድራለሁ፤

ይእተ፡ አሚረ፡ እክዑ፡ እምነ፡ መንፈስየ፤

ያን፡ ጊዜ፡ በሰባ፡ ዘመን፡ ረድኤቴን፡ በሁሉ፡ አሣድራለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፤ ወእገብር፡ ተአምረ፡ በሰማይ፡ በላዕሉ፡ ወበምድር፡ በታሕቱ፤

ከምድር፡ በላይ፡ ባለ፡ በሰማይ፤ ከሰማይ፡ በታች፡ ባለ፡ በምድር፡ ተአምራት፡ አደርጋለሁ፡ ማለት፡ በዔዋዌ፡ የእስራኤል፡ ልዑላኑ፤ ትሑታኑ፡ ይማረካሉ፤ አንድም፡ በሚጠት፡ የአሕዛብ፡ ልዑላኑ፡ ትሑታኑ፡ ይማረካሉ፤

ደመ፡

በዔዋዌ፡ የእስራኤል፡ ደማቸው፡ ይፈስሳል፤ አንድም፡ በሚጠት፡ የአሕዛብ፡ ደማቸው፡ ይፈስሳል፤

ወእሳተ፤

በዔዋዌ፤ የእስራኤል፡ ቤታቸው፡ ይተኮሳል፤ አንድም፡ በሚጠት፡ የአሕዛብ፡ ቤታቸው፡ ይተኮሳል፤

ወተነ፡ ጢስ፤

እሳት፡ ካለ፡ ዘንድ፡ ተንታ፡ (ትንታግ) አይታጣምና፤

፴፩፤ ፀሐይኒ፡ ይጸልም፤

ሊቀ፡ ካህናቱ፡ ይጠፋል፤

ወወርኅኒ፡ ደመ፡ ይከውን፤

የእስራኤል፡ ንጉሡ፡ ይጠፋል፤ አንድም፡ ፀሐይኒ፡ የአሕዛብ፡ ንጉሡ፡ ይጠፋል፤ ወወርኅኒ፤ የአሕዛብ፡ ቢትወደዱ፡ ይጠፋል፤

ዘእንበለ፡ ትብጻሕ፡ ዕለተ፡ እግዚአብሔር፡ ዓባይ፡ እንተ፡ ታስተርኢ፤

ጭንቅ፡ የምትሆን፡ ዕለተ፡ ዔዋዌ፡ ሳትደርስ፤

፴፪፤ ወኵሉ፡ ዘጸውዐ፡ ስመ፡ እግዚአብሔር፡ ይድኅን፤

የእግዚአብሔርን፡ ስም፡ የሚጠሩ፡ ነቢያት፡ ካህናት፡ ይድናሉ፤ አንድም፡ የምትገለጥ፡ ዕለተ፡ ሚጠት፡ ሳትደርስ፡ ስመ፡ እግዚአብሔርን፡ የሚጠሩ፡ ትሩፋን፡ ይድናሉ፤ አንድም፡ ወእገብር፡ ተአምረ፡ በሰማይ፡ ብለህ፡ መልስ፤ በዕለተ፡ ስቅለት፡ በሰማይ፡ በምድር፡ ተአምራት፡ አደርጋለሁ፤ የጌታ፡ ደም፡ ይፈስሳል፡ ምድር፡ ሳለው፤ ወእሳተ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ይሰጣል፤ ሰማይ፡ ላለው፤ ወተነ፡ ጢስ፤ ሀብቱ፡ ብዙ፡ ነውና፤ ይኸንስ፡ ያመጣዋል፡ ብሎ፡ ወእሳተ፤ ትኩስ፡ ነውና፤ ወተነ፡ ጢስ፤ ትኩስነት፡ ካለ፡ ዘንድ፡ ተንታ አይጠፋምና፤ አንድም፡ በሰማያዊ፡ መለኮት፡ በምድራዊ፡ ትስብእት፡ ምልክት፡ አሳያለሁ፤ ደመ፡ ወእሳተ፤ አይለወጥም፤



ፀሐይ፡ ይጨልማል፤ ጨረቃ፡ ደም፡ ይሆናል፤ ሰማይ፡ ላለው፡ አመጣ፤ ዕለተ፡ ትንሣኤ፡ ሳትደርስ፡ ስመ፡ እግዚአብሔርን፡ የሚጠራ፡ ፈያታዊ፡ ዘየማን፡ ይድናል፤ አንድም፡ ጌታ፡ በተሰቀለ፡ በአርባ፡ ዘመን፡ በሰማይ፡ በምድር፡ ተአምራት፡ ይደረጋል፤ ከዋክብት፡ በሰማይ፡ ተሰልፈው፡ ሲዋጉ፤ ታይተዋል፤ አንድም፡ መላእክት፡ በሰማይ፡ ተሰልፈው፡ ሲዋጉ፡ ታይተዋል፤ በሮም፡ አንጻር፡ ያሉ፡ መላእክት፡ ድል፡ ሲነሱ፤ በኢየሩሳሌም፡ አንጻር፡ ያሉ፡ መላእክት፡ ድል ሲነሱ፡ ታይተዋል፤ ይኸንን፡ ምልክት፡ አድርገው፡ ሮማውያን፡ መጥተው፡ አጥፍተዋቸዋል፤ አንድም፡ እንደበለው፡ ጊዜ፡ ጅራታም፡ ኮከብ፡ ታይቷል፤ ይህ፡ ሰማይ፡ ላለው፡ ነው፤ ለመሥዋዕት፡ ያቀረቧት፡ ጊደር፡ በግ፡ ፀንሳ፡ ተገኝታለችና፤ ቃላተኛም፡ ይዔወዉ፡ (ይዔወው)፡ ብሎ፡ ተናግሮባቸዋልና፡ ግሁስም፡ በአደባባይ፡ ቃላት፤

በውስተ፡ መራሕብት፡ ቃላት፡ በውስተ፡ አናቅጽ፡ ቃላት፡ ብሎ፡ ሲናገር፡ ተሰምቷል፤ በሸበተም፡ ደንጋይ፤ ንጉሥ፡ አሕዛብ፡ ይከውን፡ ንጉሥ፡ እስራኤል፡ የሚል፡ ተጽፎ፡ ተገኝቷል፤ እንዲህ፡ ማለቱ፡ ጥጦስ፡ ይነግሥባቸዋል፡ ሲል ነው፤ እነ ዚያ፡ ግን፡ ዘሩባቤል፡ የሚነግሥልን፡ መስሏቸው፡ አምስቱን፤ ቆመ፡ ብእሲ፤ ስድስቱን፤ ቆመ፡ ብእሲ፤ ፈጥነው፡ ሠርተዋል፤በአርባ፡ ዘጠኝ፡ ዘመን፡ በኢዮቤልዩ፡ ለአምሳ፤ ለስድሳ፡ የሚከፈቱ፡ መዝጊያዎች፤ ሀለወነ፡ ንትረኀው፤ እያሉ፡ እየተከፈቱ፡ ተገኝተዋል፤ ምድር፡ ላለው፤ አንድም፡ የአይሁድ፡ ልዑላኑ፡ትሑታኑ፡ ይጠፋሉ፤ የአይሁድ፡ ደማቸው፡ ይፈስሳል፤ ቤታቸው፡ ይተኮሳል፤ እሳት፡ ካለ፡ ዘንድ፡ ተንታ፡ አይጠፋምና፤ ፀሐይ፡ ይጨልማል፤ ጨረቃ፡ ደም፡ ይሆናል፤ በወልደ፡ እግዚአብሔር፡ ባደረጉት፡ ፍዳ፡ እንደመጣባቸው፡ ለማጠየቅ፡ በዕለተ፡ ዓርብ፡

www.ethiopianorthodox.org

የተደረገው፡ ተደርጎባቸዋል፤ ዕለተ፡ ምጽአት፡ ሳትደርስ፡ ስመ፡ እግዚአብሔርን፡ የጠራ፡ ይድናል፤ ስምዖን፡ የሚባል፡ ኤጲስ፡ ቆጶስ፡ ሰብአ፡ ረበዋትን፡ ይዞ፡ ድኗል፤

እስመ፡ በደብረ፡ ጽዮን፡ ወበኢየሩሳሌም፡ ይድኅኑ፡ በከመ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ እለይሜሕሩ፡ እለ፡ እግዚአብሔር፡ ጸውዖሙ፤

በደብረ፡ ጽዮንና፡ በኢየሩሳሌም፡ የሚኖሩ፡ ስመ፡ እግዚአብሔርን፡ ጠርተው፡ ይድናሉ፡ ብሏልና፤ አንድም፡ እግዚአብሔር፡ የመረጣቸው፡ ሕጉን፡ የሚያስተምሩ፡ ነቢያት፡ በኢየሩሳሌም፡ ይኖራሉ፤ አንድም፡ ሕጉን፡ የሚያስተምሩ፡ ሐዋርያት፡ በኢየሩሳሌም፡ ይኖራሉ፤ አንድም፡ ሕጉን፡ የሚያስተምሩ፡ ሄኖክ፡ ኤልያስ፡ በደብረ፡ ጽዮን፡ ይኖራሉ።

## ምዕራፍ ፫

፩፤ እስመ፡ ይእቲ፡ አሚረ፡ አነ፡ በእማንቱ፡ መዋዕል፡ እመይጥ፡ ፄዋ፡ ይሁዳ፡ ወኢየሩሳሌም፤

እኔ፡ ያንጊዜ፡ በዚያ፡ ወራት፡ የዐሥሩን፡ ነገድ፤ የሁለቱን፡ ነገድ፡ ምርኮ፡ እመልሳለሁ፡ ብሏልና፤ አንድም፡ የይሁዳ፡ ዘነፍስን፡ ምርኮ፡ እመልሳለሁ፡ ብሏልና፡ እሉ፡ ይሜህሩ፡ ኋለው፤

፪፤ ወአስተጋብኦሙ፡ ለኵሎሙ፡ አሕዛብ፡ ወአወርዶሙ፡ ቈላተ፡ ዮሳፍጥ፤

አሕዛብን ሰብስቤ፡ ወደሚጠፉበት፡ ቦታ፡ አወርዳቸዋለሁ፤

ቈላተ፡ ዮሳፍጥ፡ ማለት፡ ቈላተ፡ ሥራዊ፡ ማለት፡ ነው፤

ወእትዋቀሶሙ፡ በህየ፡ በእንተ፡ ሕዝብየ፡ ወበእንተ፡ ርስትየ፡ እስራኤል፤

ስለ፡ ወገኖቼ፡ ስለማደሪያዎቼ፡ ስለቤተ፡ እስራኤል፡ በዚያ፡ እወቅሳቸዋለሁና፤

በነበ፡ ተዘርዉ፡ በውስተ፡ አሕዛብ፤

በተበተኑበት፡ በአሕዛብ፡ አገር፡ ሁሉ፡ እወቅሳቸዋለሁ፤

ወይትካፈሉ፡ ምድርየ፤

ኢየሩሳሌምን፡ ይካፈሏታል፤

፫፤ ወተዓፀዉ፡ ዲበ፡ ሕዝብየ፤

በወገኖቼ፡ ላይ፡ እጣ፡ ተጣጣሉ፤

ወወሀቡ፡ ደቂቆሙ፡ ለዘማት፡ በሤጥ፤

ወንዶች፡ ልጆቻቸውን፡ ለሴሰኞች፡ ሴቶች፡ በዋጋ፡ ሸጡ፤

ወአዋልዲሆሙኒ፡ ለወይን፡ወሰትዩ፤

ሴቶች፡ ልጆቻቸውንም፡ ለመሸታ፡ ሸጠው፡ ጠጡ፤



፬፤ ምንት፡ ብየ፡ ምስሌክን፡ ጢሮስ፡ ወሲዶና፤

የእስራኤልን፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ተናግሮ፡ የኛን፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ሳይናገር፡ ቀረ፡ ትሉኝ፡ እንደ ሆነ፡ ጢሮስ፡ ሲዶና፡ ከናንተ፡ ምን፡ ፍቅር፡ አለኝ፤

ወኵሉ ገሊላ፡ ዘኢሎፍሊ፤

የኢሎፍሊ፡ ክፍል፡ ከምትሆን፡ ገሊላ፡ ሁሉ፡ ምን፡ ፍቅር፡ አለኝ፤

በቀለ፡ እትቤቀለክን፡ ወቂመ፡ እትቄየመክን፡ ፍጡነ፤

እናንተንስ፡ ተበቅዬ፡ ተቀይሜ፡ ፈጥኜ፡ አጠፋችኋለሁ፤

ወበጕጕአ፡ እፌድየክሙ፡ ፍዳክሙ፡ ዲበ፡ ርእስክሙ፤

ፈጥኜ፡ መከራውን፡ በራሳችሁ፡ ላይ፡ አመጣባችኋለሁ፤

፭፤ ናሁ፡ ነሣእክሙ፡ ወርቅየ፡ ወብሩርየ፡ ወአሥራትየ፡ ወመሠንዮ፡ አባዕክሙ፡ ቤተክሙ፤

ምን፡ ሰምተህብናል፡ ትሉኝ፡ እንደሆነ፡ ወርቁን፤ ብሩን፤ አሥራቱን፡ የአማረውን፡ ገንዘብ፡ ሁሉ፡ ወስዳችሁ፡ ከቤታችሁ፡ አገባችሁት፤ አንድም፡ በተፈጥሮ፡ ገንዘቡ፡ ነውና፡ ወርቁን፡ ብሬን፡ አሥራቱን፡ ከቤታችሁ፡ አገባችሁት፤

፮፤ ወሜጥክምዎሙ፡ ለደቂቀ፡ ይሁዳ፡ ወለደቂቀ፡ ኢየሩሳሌም፡ ኀበ፡ ደቂቀ፡ አረሚ፤

የዐሥሩን፡ ነገድ፡ የሁለቱን፡ ነገድ፡ ልጆች፡ ለዕርአውያን፡ ልጆች፡ ለመሸታ፡ ሸጣችኋቸው፤ አንድም፡ ኀበ፡ ደቂቀ፡ ዮናናውያን፡ ይላል፤ ለዕርአውያን፡ ልጆች፡ ማለት ነው፤

ከመ፡ ታጥፍዕዎሙ፡ እምሀገሮሙ፤

ከሀገራቸው፡ ታጠፏቸው፡ ዘንድ፤

፯፤ ወናሁ፡ አነ፡ አነሥኦሙ፡ እምውእቱ፡ ብሔር፡ ኀበ፡ ሜጥክምዎሙ፡ ህየ፤

እነሆ፡ እኔ፡ ከዚያ፡ ከሸጣችሁበት፡ አገር፡ አመጣቸዋለሁ፤

ወእፌድየክሙ፡ ፍዳክሙ፡ ዲበ፡ ርእስክሙ፤

ፍዳውንም፡ በራሳችሁ፡ አመጣባችኋለሁ፤

፰፤ ወእትቤቀሎሙ፡ ለደቂቅክሙ፡ ወለአዋልዲክሙ፡ በእዴሆሙ፡ ለደቂቀ፡ ይሁዳ፤

ወንዶች፡ ልጆቻችሁን፡ ሴቶች፡ ልጆቻችሁን፡ በእስራኤል፡ ልጆች፡ እጅ፡ እበቀላቸዋለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእትቤቀለክሙ፡ በነበ፡ ተዔወውክሙ፡ በውስተ፡ አሕዛብ፡ ርኁቃን፡ ወነዊሃን፨

ተማርካችሁ፡ በሄዳችሁበት፡ በአሕዛብ፡ ዘንድ፡ ፈጽሜ፡ እበቀላችኋለሁ፤

፱፤ እስመ፡ እግዚአብሔር፡ ነበበ፡ ሰብኩ፡ ዘንተ፡ ውስተ፡ አሕዛብ፨

እግዚአብሔር፡ ይኸንን፡ በአሕዛብ፡ ዘንድ፡ አዋጅ፡ ንገሩ፡ ብሎ፡ ተናግሯልና፤

ወዐሥሩ፡ ፀብዐ፨

ሰልፍ፡ እናድርግ፡ ብላችሁ፡ ቀን፡ ቅጠሩ፤

ወአንሥኡ፡ መስተቃትላነ፡ ወአውፅዕዎሙ፨

አርበኞችን፡ ከቤታቸው፡ አስወጥታችሁ፡ ስደዱ፤

ወይዕርጉ፡ ኵሎሙ፡ ዕደው፡ መስተቃትላን፨

አርበኞች፡ ሁሉ፡ ወደ፡ ሰልፍ፡ ይውጡ፤

፲፤ ወማኅረሰክሙ፡ አግብሩ፡ ኵያንወ፨

ማረሻውን፡ ጦር፡ አድርጋችሁ፡ አሠሩት፤

ወማዕፀድክሙኒ፡ አግብሩ፡ ረምሐ፨

ማጭዳችሁንም፡ ዘገር፡ አድርጋችሁ፡ አሠሩት፤

ድኩምኒ፡ ለይብል፡ ጽኑዕ፡ አነ፨

ደካማውም፡ እኔ፡ ብርቱ፡ ነኝ ይበል፤

፲፩፤ ወይትጋብዑ፡ ኵሉ፡ አሕዛብ፨

አሕዛብ፡ ሁሉ፡ ወደሚጠፉበት፡ ቦታ፡ ይሰብሰቡ፤

ወይሑሩ፡ ይዕግቱ፨

ይከቡ፡ ዘንድ፡ ይሂዱ፤

ወይትጋብዑ፡ ህየ፨

በዚያ፡ ይሰብሰቡ፤

የዋሃን፡ ይኩኑ፡ መስተባዕላነ፨

የጦር፡ ሰልፍ የማያውቁ፡ ሰዎች፡ የጦር፡ ሰልፍ የሚያውቁ፡ ይሁኑ፤

፲፪፤ ወይትነሥኡ፡ ኵሉ፡ አሕዛብ፡ ወይዕርጉ፡ ውስተ፡ ቈላተ፡ ዮሳፍጥ፨

አሕዛብ፡ ሁሉ፡ ተነሥተው፡ ወደሚጠፉበት፡ ቦታ፡ ይውጡ፤

እስመ፡ ህየ፡ እነብር፡ ወእትዋቀሶሙ፡ ለኵሎሙ፡ አሕዛብ፨

ከዚያ፡ ተቀምጬ፡ አሕዛብን፡ ሁሉ፡ እወቅሳቸዋለሁና፤

፲፫፤ ወእለ፡ አድያም፡ ፈንዉ፡ ማዕፀደ፡ እስመ፡ በጽሐ፡ ማዕረር፨

መከሩ፡ ደርሷልና፡ በዙሪያችሁ፡ ወዳሉ፡



ባሉ፡ ወኪዱ፡ እስመ፡ መልዐ፡ ምክያድ፨

አውድማው፡ ሞልቷልና፡ ገብታችሁ፡ አበራዩ፤

ወተክዕወ፡ እምነ፡ ምክያድ፨

ከአውድማውም፡ መልቶ፡ ትርፍርፍ፡ ብሏልና፤ አንድም፡ ወእለ፡ አድያም፡ ብለህ፡ መልስ፨ በዙሪያችሁ፡ ወዳሉ፡ አገሮች፡ ጦር፡ ስደዱ፡ በሚጠፉበት፡ ቦታ፡ በዝተው፡ ተሰብስበዋልና፡ ገብታችሁ፡ አጥፏቸው፤

ናሁ በዝኃ፡ እከዮሙ፨

እነሆ፡ ክፋታቸው በዛ፤

፲፬፤ ወወውዑ፡ በቈላተ፡ ቅሥት፨

ፀብ፡ ክርክር፡ በሚደረግበት፡ ቦታ፡ ደንፉ፡ አግሩ፤

ወድምፁ፨

ገድላችሁ፡ ሰልባችሁ፡ ስትደነፉ፡ ሰዎች፡ ይስሟችሁ፤

እስመ፡ አልጸቀት፡ ዕለተ፡ እግዚአብሔር፡ በውስተ፡ ቈላተ፡ ቅስት፨

ፀብ፡ ክርክር፡ በሚደረግበት፡ ቦታ፡ እግዚአብሔር፡ አሕዛብን፡ የሚያስማርክበት፡ ቀን፡ ደርሷልና፤

፲፭፤ ፀሐይ፡ ወወርኅ፡ ይጸልሙ፨

የአሕዛብ፡ ንጉሡ፡ ቢትወደዱ፡

ወሰከዋክብትኒ፡ የዓርብ፡ ብርሃኖሙ፨

የሠራዊቱም፡ ተድላቸው፡ ደስታቸው፡ ይጠፋል፤

፲፮፤ ወይኬልሕ፡ እግዚአብሔር፡ እምጽዮን፡ ወእምኢየሩሳሌም፡ ይሁብ፡ ቃሎ፨

እግዚአብሔር፡ በነቢያት፡ በካህናት፡ አድሮ፡ ያናግራል፤

ወያድለቀልቁ፡ ሰማይ፡ ወምድር፨

ልዑላኑ፡ ትሑታኑ፡ በመከራ፡ ይነዋወጣሉ፤

ወእግዚአብሔር፡ ይምሕክ፡ ሕዝቦ፨

እግዚአብሔር፡ ግን፡ ለወገኖቹ፡ ይራራል፤

ወያጸንዖሙ፡ እግዚአብሔር፡ ለደቂቀ፡ እስራኤል፨

እግዚአብሔር፡ የእስራኤልን፡ ልጆች፡ በረድኤት፡ ያጸናቸዋል፤

፲፯፤ ወተአምሩ፡ እንከ፡ ከመ፡ አነ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክክሙ፡ ዘአኃድር፡ ውስተ፡ ጽዮን፡ ደብረ፡ መቅደስየ፨

በመመስገኛዬ፡ ቦታ፡ በቤተ፡ መቅደስ፡ የምኖር፡ ፈጣሪያችሁ፡ እኔ፡ እንደሆንሁ፡ ታውቃላችሁ፤

ወትከውን፡ ኢየሩሳሌም፡ ሀገረ፡ ቅድስተ፨

ኢየሩሳሌም፡ ክብርት፡ አገር፡ ትሆናለች፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኢየኃልፍ፡ እንከ፡ ውስቴታ፡ ዘእምነ ልዕ፡ ሕዝብ፡

ከራቀ፡ ከአሕዛብ፡ ወገን፡ የሚ ሆን፡ በእሷ፡ አይሄድም፤ አን ድም፡ ሰይጣን፡ በምእመናን፡ አያድርም፤

፲፰፤ ወይከውን፡ ይእቲ፡ አሚረ፣

ያን፡ ጊዜ፡ እንዲህ፡ ይሆናል፤

ያንጸፈጽፍ፡ መዓር፡ እምአድባር፡ ወይ ውኅዝ፡ ሀሊብ፡ እምአውግር፡ ወይነቅዕ፡ ማይ፡እምኵሉ፡በሐውርተ፡ ይሁዳ፣

ይከውን፡ ያለውን፡ ያንጸፈጽፍ ብሎ፡ አመጣው፣ ያንጊዜ፡ በሚ ጠት፡ ማሩ፡ ከተራራ፡ ወተቱ፡ ከኮረብታ፡ ይፈስሳል፡ ማለት፡ ሰዎች፡ ተሸክመው፡ ሲመጡ፡ ከብዛቱ፡ የተነሣ፡ ይፈስሳል፤ አንድም፡ ከላሚቱ፡ ጡት፡ ይነ ዛል፤ አንድም አድባር፡ ከነገ ሥታት፡ ከመኳንንት፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ይገኛል፣ ወይነቅዕ፣ ከነ ቢያት፡ ትምህርት፡ ይገኛል፤ አንድም፡ መዓር፡ ኦሪት፣ ሀሊብ፡ ወንጌል፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ይነገ ራሉ፤ አንድም፡ አድባር፡ በሐ ዋርያት፡ ኦሪት፣ በአርድእት፡ ወንጌል፡ ትነገራለች፣ ማካፈል፡ አይደለም፣ በሐዋርያት፡ ኦሪት፡ ወንጌል፣ በአርድእት፡ ኦሪት፡ ወንጌል፡ ይነገራሉ፤ አንድም፡ ከጳጳሳት፣ ከሊቃነ፡ ጳጳሳት፣ ከኤጲስ፡ ቆጶሳት፡ ትምህርት፡ ልጅነት፡ ይገኛል፣ በይሁዳ፡ አውራጃ፡ ሁሉ፡ ምንጭ፡ ይመ ነጫል፤ አንድም፡ ዐሥርቱ፡ ቃላት፡ ሕገ፡ ወንጌል፡ ይነገራሉ፤

ወይፈለፍል፡ ነቅዕ፡ እምቤተ፡ እግዚአብሔር፣

ከቤተ፡ እግዚአብሔር፡ ምንጭ፡ ይመነጫል፤ አንድም፡ ከቤተ፡ እግዚአብሔር፡ ሥጋው፡ ደሙ፡ ይገኛል፤

ወይሰቂ፡ ፈለገ፡ ሰኪኖን፣

ኮኩ፡ ውሀውን፡ ይጠጣል፤ አን ድም፡ ወይሰቂ፡ ፈለግ፡ ሰኪኖን፡ ውሀው፡ ኮኩን፡ ያጠጣል፤ አን ድም ደቀ፡ መዝሙር፡ ትምህ ርቱን፡ ይቀበላል፤ አንድም፡ ነቢያት፡ ካህናት፡ እስራኤልን፡ ያስተምራሉ፣ እስራኤል ለእ ግዚአብሔር፡ ምግባር፡ ሃይማ ኖት፡ ያቀርባሉ፤ አንድም፡ ምእ መናን፡ ምግባር፡ ሃይማኖት፡ ያቀርባሉ፣ ሰኪኖን፡ ቢል፡ ሐዋ ርያት፡ ምእመናንን፡ ያስተምራሉ፣

፲፱፤ ወይማስን፡ ብሔረ፡ ግብፅ፣

የግብፅ፡ አውራጃ፡ ሁሉ፡ ይጠፋል፤



ወይከውን፡ በድወ፣

ምድረ፡ በዳ፡ ይሆናል፤

ወኤዶምያስኒ፡ ይጠፍዑ፡ በኃጢአቶሙ፡ በእደዊሆሙ፡ ለደቂቀ፡ ይሁዳ፣

የኤዶምያስ፡ ሰዎች፡ የይሁዳን፡ ልጆች፡ ስለበደሉ፡ በኃጢአታ ቸው፡ ምክንያት፡ ይጠፋሉ፤ አንድም፡ በኢያሱ፡ በዳዊት፡ በሕ ርቃሎስ፡ ጊዜ፡ ይጠፋሉ፤

እስመ፡ ከዓዉ፡ ደመ፡ ጻድቅ፡ ውስተ፡ ምድሮሙ፣

የደጉን፡ ሰው፡ ደም፡ በሀገራ ቸው፡ አፍስሰዋልና፤

፳፤ ወይሁዳሰ፡ ለዓለም፡ ትነብር፣

ይሁዳ፡ ግን፡ ለዘለዓለሙ፡ ትኖራለች፤

ወኢየሩሳሌምኒ፡ ለትውልደ፡ ትውልድ፣

ኢየሩሳሌምም፡ ለልጅ፡ ልጅ፡ ዘመን፡ ትኖራለች፤

፳፩፤ ወእትቤቀል፡ ደሞሙ፡ ወኢያነጽሕ፣

ደማቸውን፡ እበቀላለሁ፣ ከፍዳ፡ አላነጻቸውም፤

እስመ፡ አነ፡ እግዚአብሔር፡ ዘአኃድር፡ ውስተ፡ ጽዮን፣

በጽዮን፡ ሰማያዊት፡ በጽዮን፡ ምድራዊት፡ የምኖር፡ እኔ፡ ነኝና፤

ተፈጸመ፡ ዘኢዩኤል፡ ነቢይ፣

ኢዩኤል፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ደረሰ፡ ተፈጸመ፣

በረከተ፡ አምላኩ፡ የሃሉ፡ ምስሌነ፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፣

አነቃቅቶ፡ ለአስጀመረን፡ አተ ጋግቶ፡ ለአስፈጸመን፡ ለእግዚ አብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግ ባው፣ አሜን፡፡

www.ethiopianorthodox.org